

# እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ምስለ ፍቁር ወልዳ

Copyright © 2009 Debre Selam Medhanealem Ethiopian Orthodox Tewahedo Church 4401 Minnehaha Avenue South Minneapolis, Minnesota 55406 Tel. (612) 721-1222 (U.S.A)

# ነገረ ማርያም

## መግቢያ፡-

### ፩. የቅድስት ድንግል ማርያም የትውልድ ሐረግ

እግዚአብሔር አምላክ ማደሪያው ሁሉ ንጹሕና ቅዱስ ፍጹምም ነው።ስለሆነም እርሱ ያደረበት ሰውም ሆነ ቦታ ወይንም ነዋይ ሁሉ ቅዱስ ይባላል። እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም የአምላክ ማደሪያ ሆና ስለተገኘች ቅድስት ትባላለች ። የተገኘችውም እግዚአብሔር ካደረባቸው ቅዱሳን ስለሆነም ጭምር ቅድስት ተብላለች። ቅዱሳን የተባሉ ዘሮቿ እነማን ናቸው? ቢባል ከዚህ እንደሚከተለው ዋና ዋናዎቹን እናያቸዋለን፡-

አዳም → ሴት → ኖኅ → ሴም → አብርሃም → ይስሐቅ

→ ያዕቆብ → ይሁዳና ፤ ሌዊ → ዳዊት → ሰሎሞን → ጰጥርቃና/ቴክታ

→ ኢያቄም/ሐና → ድንግል ማርያም → ኢየሱስ ክርስቶስ።

#### ሀ. አብርሃም፡-

አባታችን አብርሃም ቅዱስ የእግዚአብሔር ሰው ነበር እግዚአብሔር አምላክም አስቀድሞ ቃል የገባለት ወይንም የመረቀው ሰው ነው "ዘርህንም እንደ ሰማይ ከዋክብት በባሕር ዳር እንዳለ አሸዋ አበዛዋለሁ" ብሎ እግዚአብሔር ቃል ኪዳን የሰጠው ጻድቅ ሰው ዘፍ.፳፪ ፥፲፯። በዕብራውያን መልዕክቱ ፪ ፥፲፮ ላይ ቅዱስ ጳውሎስ ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ሲናገር "የአብርሃምን ዘር ይዟል እንጂ የመላእክትን አይደለም" በማለት ከአብርሃም ዘር በወረደው የሰው ዘር በኩል እንደተወለደ መስክሯል።

#### ለ. ዳዊት፡-

ወንጌላዊው ቅዱስ ማቴዎስ የኢየሱስን ክርስቶስን የትውልድ ሐረግ በፃፈበት በምዕራፍ ፩ ላይ "የዳዊት ልጅ የአብርሃም ልጅ የኢየሱስ ክርስቶስ የትውልድ መጽሐፍ" ብሎ ይጀምራል ፤ ስለቅዱስ ዳዊት እግዚአብሔር ሲመሰክርለትም "እንደልቤ የሆነ ሰው ፈቃዴንም ሁሉ የሚያደርግ የእሴይን ልጅ ዳዊትን አገኘሁ" ሐዋ.ሥራ ፲፫ ፥፳፪ ብሎ የጠራው ታላቅ ቅዱስ የእግዚአብሔር ባለሟል ነው

#### ሐ. ኢያቄም እና ሐና፡-

የቅድስት ድንግል ማርያም አባትና እናት ናቸው እነዚህ ባልና ሚስት ሕይወታቸውን በተቀደሰ ኑሮ እየመሩ በኢየሩሳሌም አካባቢ ይኖሩ የነበሩ ሰዎች ናቸው ፤ ሕይወታቸው በእግዚአብሔር የሚመራ ቅዱሳን ቢሆኑም ልጅ አልነበራቸውም ፤ በዚህ ምክንያት በተለይ ቅድስት ሐና ከጎረቤቶቿና ከአካባቢው ሴቶች ሽሙጥና መገለል ይደርስባት ነበር ፤ ይህም በዚያን ጊዜ ያልወለደች ሴት እንደ ኃጢአተኛ ትቆጠር ስለነበር ነው። በዚህ የተነሣ ቅድስት ሐና ዘወትር ወደ ፈጣሪዋ ልጅ ይሰጣት ዘንድ ትጸልይ ነበር ፤ ብጽአትም ወይም ስእለት ገብታ አምላኳን ተማጸነች ፤ ብጽአቷም ወንድ ልጅ ከሰጣት ካህን ቀዳሽ የእግዚአብሔርን ቤት አገልጋይ እንዲሆን ፤ ሴትም ብትሆን ውሃ ቀድታ ፤ ፈትል ፈትላ ፤ ቤተ እግዚአብሔርን እንድታገለግል ለቤተመቅደስ ልትሰጣት ነበር። የሰዎችን ልመና የማይንቅ እግዚአብሔርም ልመናዋን ሰማት ፤ ልጅም ፀነሰች ፤ ይህም የሆነው ነሐሴ ፯ ቀን ከክርስቶስ ልደት በፊት ፲፮ ዓመት ላይ ነበር እመቤታችንም ግንቦት ፩ ቀን ፲፭ ዓመት ቅድመ ክርስቶስ ሊባኖስ

Copyright © 2009 Debre Selam Medhanealem Ethiopian Orthodox Tewahedo Church 4401 Minnehaha Avenue South Minneapolis, Minnesota 55406 Tel. (612) 721-1222 (U.S.A)

በተሰኘ ቦታ ተወለደች። በአጠቃላይ እንደነዚህ ካሉ ቅዱሳን ዘር የተገኘች በመሆኗ እመቤታችን ቅድስት ተብላለች። ነብዩ ዳዊት በመዝሙር ፹፮ ፥፩ ላይ "መሠረቶቿ በተቀደሱ ተራሮች ናቸው" ሲል ስለ ትውልዷ ይመሰክራል።

## ጥያቄ፦

ከላይ የተማርነውንና ያነበብነውን መሠረት በማድረግ ትክክለኛውን መልስ ስጥ/ጪ.

፩. አብርሃም ከወለዳቸው ልጆች የኢየሱስ ክርስቶስ የትውልድ ሐረግ የወረደው በየትኛው በኩል ነው?
   ሀ. በእስማኤል ለ. በይስሐቅ ሐ. በሁለቱም

፪. ከያዕቆብ ልጆች በድንግል ማርያም የትውልድ ሐረግ ገብተው የተቆጠሩት እነማን ናቸው?

   ሀ. ዮሴፍና ይሳኮር ለ. ሌዊና ዮሴፍ ሐ. ይሁዳና ሌዊ መ. ሁሉም

፫. ለሚከተለው ጥያቄ ማብራሪያ ስጥ/ስጪ.

ቅዱስ ዳዊት "መሠረቶቿ በተቀደሱ ተራሮች ናቸው" ሲል የተቀደሱ ተራሮች የሚለው ማንን ነው? ለምን?

፬. ለሚከተለው ጥያቄ እውነት/ሐሰት በማለት መልስ/ሽ
ቅድስት ድንግል ማርያም ለእናትና አባቷ የበኲር ልጅ ናት።

   ሀ. እውነት ለ. ሐሰት

፭. እመቤታችን ለምን ቅድስት ተባለች?

## ፪. የድንግል ማርያም የስሟ ትርጓሜ

ማርያም ማለት በእብራይስጥ ቋንቋ ማሪሃም ከሚለው ቃል የተወሰደ ሲሆን ትርጉሙም የብዙኃን እናት ማለት ነው ፤ አብርሃም ማለት የብዙኃን አባት ማለት እንደሆነ ዘፍ. ፲፯ ፥ ፭

በቤተክርስቲያናችን ትምህርት መሠረት ማርያም የሚለው ስም እያንዳንዱ ፊደል የራሱ የሆነ ትርጉም ተሰጥቶት ይተረጎማል ይኸውም፦

ማ ማኅደረ መለኮት (የመለኮት ማደሪያ)

ር ርግብዬ ይቤላ (መኀልየ መኀልየ ሰሎሞን ፮፦፱)

ያ ያንቀዐዱ ኃቤኪ ኲሉ ፍጥረት (ፍጥረት ሁሉ ለምኝልን እያሉ ወደ አንቺ ያንጋጥጣሉ)።

ም ምስጋድ ወምስአል ወመስተሥሬየ ኃጢያት (መስገጃ መለመኛ የኃጢያት ማስተሰሪያ) ማለት ነው። ፬ዜና ፮ ፥፲፩-፲፰

ከዚህ በተጨማሪ የቤተክርስቲያናችን ሊቃውንት የቅድስት ድንግል ማርያምን ስም እንደሚከተለው ያመሰጥሩታል፦

**ሀ. ማርያም ማለት መርሕ ለመንግሥተ ሰማያት/ ወደ መንግሥተ ሰማያት መርታ የምታገባ ማለት ነው።**

የአዳም ዘር በሙሉ በኢየሱስ ክርስቶስ ቤዛነት ወደ ገነት የገባው ወይንም ወደ ቀደመ ክብሩ የተመለሰው የእርሷን ሥጋ ለብሶ በመወለዱ ስለሆነ እንዲሁም ወደ ዘለዓለም ሕይወት የሚያስገባው ቅዱስ ሥጋውና ክቡር ደሙም ከርሷ የነሣው በመሆኑ ነው። በተጨማሪም የድንግል ማርያምን አማላጅነት ሳያምኑ መንግሥተ ሰማያት መግባት አይቻልምና ነው።

**ለ. ማርያም ማለት ጸጋና ሐብት ማለት ነው፦**

የአዳምና የዘሩ ጸጋ መንፈስ ቅዱስና ኃብተ መንፈስ ቅዱስ የተመለሰው ከእመቤታችን በተገኘው/በተወለደው ሰው በሆነው አምላክ ስለሆነ የስሟ ትርጓሜ ጸጋና ሀብት ተብሏል ፤ በሉቃስ ፩ ፥፳፰ ላይም መልአኩ ቅዱስ ገብርኤል ሲያበስራት "ጸጋን የተመላሽ ሆይ ደስ ይበልሽ" ብሎ ጸጋ የመላባት መሆኗን መስክሯል።

**ሐ. ማርያም ማለት በድንጋሌ ሥጋ በድንጋሌ ነፍስ የጸናች ፍጽምት ማለት ነው**

እግዚአብሔር በባሕርዩ ፍጹም አምላክ ስለሆነ ማደሪያውም ፍጹም ነውና ከፍጥረታት ሁሉ ከመላእክትም ቢሆን በተለየ መልኩ በሥጋ ያደረባት ስለሆነች ፍጽምት ናት።

**መ. <u>ማርያም ማለት ከፍጡራን በላይ ከፈጣሪ በታች ማለት ነው</u>**

እግዚአብሔር በፈጠራቸው በመላእክትና በቅዱሳን ላይ በረድኤት ወይንም በጸጋ ነው ያደረባቸው በድንግል ማርያም ላይ ግን በረድኤትና በጸጋ ብቻ ሳይሆን ከሥጋዋ ሥጋን ፤ ከደሟ ደምን ፤ ከነፍሷ ነፍስን ነሥቶ ነው የተገለጠው/ሰው የሆነው ስለሆነም ድንግል ማርያም ከመላእክትም ከቅዱሳንም ትበልጣለችና ከፈጣሪ በታች ከፍጡራን በላይ ተብላለች

**ሠ. ማርያም ማለት የብዙዎች እናት ማለት ነው**

አንድ ቤት የቤት እመቤትና አባወራ እንዳለው ሁሉ በክርስቶስ አምነው ላሉ ክርስቲያኖች ሁሉ እመቤታቸው /እናታቸው ድንግል ማርያም ናት ፤ የቤታቸው ራስ ልጇ አማኑኤል እንደሆነ ማለት ነው።

**ረ. ማርያም ማለት በእግዚአብሔርና በሰው መካከል የምትላላክ ማለት ነው**

ለሰዎች በሥጋ ዘመዳችን ስትሆን ለፈጣሪ ደግሞ እናቱ ነች ፤ በመካከል ሆና የምታገናኝን ወይንም የምታማልደን ስለሆነች በሰውና በፈጣሪ መካከል ያለች መካከለኛ ትባላለች።

## ፫. <u>እመቤታችን የምትታወቅባቸው ተጨማሪ ስሞች</u>

- ወላዲተ አምላክ
- ኪዳነ ምሕረት

- ቤዛዊተ ዓለም
- እምነ ጽዮን
- ሰአሊተ ምሕረት

- ሶልያና
- አዶናዊት

Copyright © 2009 Debre Selam Medhanealem Ethiopian Orthodox Tewahedo Church 4401 Minnehaha Avenue South Minneapolis, Minnesota 55406 Tel. (612) 721-1222 (U.S.A)

## ጥያቄ፡-

**ከላይ የተማርነውንና ያነበብነውን መሠረት በማድረግ ትክክለኛውን መልስ ስጥ/ጪ**

፩. **ማርያም** ማለት

ሀ. ጸጋና ሃብት ማለት ነው ለ. የብዙዎች እናት ማለት ነው

ሐ. ኃጢያት የምታስተሰርይ ማለት ነው መ. ሁሉም መልስ ነው

፪. ከሚከተሉት **የድንግል ማርያም** ሌላ ስም የሆነው የቱ ነው ?

ሀ. ቤዛዊተ ዓለም ለ. የአርሴማ እመቤት

ሐ. ወለተ ድንግል መ. ሁሉም

፫. **የድንግል ማርያምን** የስሟን ፊደላት ትርጉም በዝርዝር ጻፍ/ጻፊ

፬. **ድንግል ማርያም** ከቅዱሳንም ከመላእክትም ትበልጣለች የተባለው እንዴት ነው ?

## ፬. ቅድስት ድንግል ማርያም በመጽሐፍ ቅዱስ

### ፩. በብሉይ ኪዳን

**እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም** በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በብዙ ቦታዎች በብዙ ምሳሌና በግልጽ የተነገረላት እመቤት ናት ፤ በብሉይ ኪዳን ከተነገሩላት ምሳሌዎች መካከል ጥቂቶቹን ብቻ ከዚህ ቀጥሎ እንመለከታለን፡-

#### ሀ. የመጀመሪያይቱ ምድር

**እግዚአብሔር አምላክ** በመጀመሪያ ምድርን ከፈጠረ በኋላ ለሰው ሕይወትን የሚሰጥ ፍሬ ያፈራችው ዘር ተዘርቶባት ሳይሆን እንዲሁ በቃሉ ብቻ መልካም የሆነውን ፍሬ እንድታፈራ ይሆን ስላለ ነው። ዘፍ.፩ ፥፲፩ **ቅድስት ድንግል ማርያምም** ልጇን **ኢየሱስ ክርስቶስን** የጸነሰችውና የወለደችው ፤ እውነተኛውን የሕይወት ፍሬ ያፈራችው በመልአኩ ቅዱስ ገብርኤል የብስራት ቃል ብቻ ስለሆነ የመጀመሪያይቱን ምድር ትመስላለች።

#### ለ. ዕጸ ሳቤቅ

**እግዚአብሔር** የአብርሃምን የእምነት ጽናት ለመለካት ልጁን ይስሐቅን ይሰዋለት ዘንድ አዘዘው ፤ አብርሃምም **አምላኩን እግዚአብሔርን** በእውነትና በፍጹም ያመልክ ስለነበር የፈጣሪውን ትእዛዝ ሊፈጽም ወደ ሞሪያ ተራራ ልጁን ይስሐቅን ይዞ ወጣ ፤ ሰይፋንም መዝዞ ልጁን ይስሐቅን ለማረድ ሲዘጋጅ **በእግዚአብሔር** መልአክ እጅ የተያዘ በዕጸ-ሳቤቅ (ሐረግ) የታሰረ በግ እንዲሠዋ ይስሐቅን እንዳይገድል **ከእግዚአብሔር** ቃል መጣ ከዚያም በጉን ሰዋው ይስሐቅም ዳነ። ዘፍ. ፳፪ ፥፩-፲፫

በዚህ ታሪክ ውስጥ ብዙ ምሳሌዎች ተነግረዋል ፤ ቅድስት ድንግል ማርያም የተመሰለችው በእጸ-ሳቤቅ (ሐረግ) ነው ፤ በበጉ ደግሞ ልጇ ኢየሱስ ክርስቶስ በጉ በሐረጉ ታስሮ እንደተገኘ **ኢየሱስ ክርስቶስም** በእርሷ ማኅፀን ተወስኖ ሰው በመሆኑ በእጸ-ሳቤቅ ትመሰላለች።

Copyright © 2009 Debre Selam Medhanealem Ethiopian Orthodox Tewahedo Church 4401 Minnehaha Avenue South Minneapolis, Minnesota 55406 Tel. (612) 721-1222 (U.S.A)

ሐ. ሰላማዊት ርግብ

በኖኅ ዘመን በደረሰው የጥፋት ውሃ ኖኅና ቤተሰቦቹ ሊድኑ የቻሉት በመርከብ ተሸሽገው ነበር ፤ ከዚያም ለመውጣት የጥፋት ውሃው መድረቁንና አለመድረቁን ለማወቅ ርግብን ላኳት እርሷም በአፏ የቄጠማ ዝንጣፊ ይዛ ተመለሰች ፤ ውሃውም እንደጎደለ አወቁ ከመርከቢቱም ወጥተው እንደገና ሰላማዊ ሕይወት መኖር ጀመሩ የላኳት ርግብ ይዛ የመጣችውና ያበሰረቻቸው ሰላምን ነው ጥፋት መወገዱን ነው ፤ እንደዚህም ሁሉ እመቤታችን ይዛ የመጣችው ኢየሱስ ክርስቶስን ነው የሰላሙን መሪ ከሰይጣን እስራት የፈታንን ስለሆነም እርሷ በርግቧ ፤ ልጇ ደግሞ በቄጠማው ይመሰላሉ።

መ. እጸ-ጳጦስ ዘሲና (የሲና ሐመልማል)

በኦሪት ዘጸአት ፫ ፥፩-፮ ላይ እንደተጻፈው ሙሴ በጎች በመጠበቅ ላይ እንዳለ በኮሬብ ተራራ ላይ ቁጥቋጦው በእሳት ሲነድ ነበልባሉ ሐመልማሉን ሳያቃጥለው አየ ፤ እርሱም ወደዚያ ለመቅረብ በፈለገ ጊዜ ከቁጥቋጦው ውስጥ የእግዚአብሔር ድምጽ ተሰማ ፤ ለሙሴም እንዲህ አለው፦ ወደዚህ ስፍራ ከመምጣትህ በፊት ጫማህን ከእግርህ አውጣ እኔ የአባትህ የአብርሃም የይስሐቅ የያዕቆብ አምላክ ነኝ ፤ ሙሴም በፍርሃት ተውጦ ፊቱን ሸፈነ ፤ ነበልባሉ ያላቃጠላት ያቺ የሲና ቁጥቋጦ ሐመልማል ምሳሌነቷ ለእመቤታችን ነው እሳት መለኮት የሆነ ጌታ እግዚአብሔር ወልድን በማሕፀኗ ይዛለችና።

ሠ. የኤልሳዕ ማሰሮ

ኤልሳዕ መምህሩ ኤልያስ በእሳት ሰረገሎች ተነጥቆ በአውሎ ንፋስ ወደ ሰማይ ከወጣ በኋላ በኢያሪኮ ተቀምጦ ሳለ የከተማይቱ ሰዎች እንዲህ አሉ ፥ እነሆ ጌታችን ሆይ የዚህች ከተማ ኑሮዋ ጥሩ ነበር ነገር ግን ውሃዋ መራራ ነው ያረገዙ ሴቶች ሲጠጡት ይጨነግፋሉ ፤ እርሱም አዲስ ማሰሮ አምጡልኝ ጨውም ጨምሩበት አላቸው። እነርሱም እንዲሁ አደረጉ ፤ እርሱም ወደ ውሃው ሄዶ ጨውን ጨመረበት ፤ ከዚህ በኋላ እግዚአብሔር ይህንን ውሃ ፈውሶታል ፤ ሞትና ጭንገፋ በዚህ ውሃ ምክንያት አይሆንም አላቸው። ፪ነገ ፪ ፥፲፱-፳፩ በአዲስ ማሰሮ የተመሰለቻው እመቤታችን ነች ፤ በጨው የተመሰለው ደግሞ ልጇ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው ፤ በመራራው ውሃ የተመሰለችው ደግሞ ይህቺ ዓለም ነች ፤ ከማሰሮው የወጣው ጨው ውሃውን እንዳጣፈጠው ከድንግል ማርያም የተገኘው እግዚአብሔር ወልድ ዓለሙን ከመራራ ኃጢያት ታድጎታል።

፪. በአዲስ ኪዳን

ሀ. የቅዱስ ገብርኤል ብስራት

"በስድስተኛው ወር መልአኩ ገብርኤል ናዝሬት ወደምትባል ወደ ገሊላ ከተማ ከዳዊት ወገን ለሆነ ዮሴፍ ለሚባል ወደ ታጨች ወደ አንዲት ድንግል ከእግዚአብሔር ዘንድ ተላከ" ሉቃ. ፩ ፥፳፮ እርሱም "...ጸጋን የተመላሽ ሆይ ደስ ይበልሽ..." እያለ በማመስገን አምላክን እንደምትወልድ አበሰራት በዚህ የቅዱስ ገብርኤል ብስራት ውስጥ ስለ እመቤታችን ድንግልናና ጸጋ የሞላባት ስለመሆንዋ ፣ የምትወልደውም አምላክ ስለመሆኑና ይህም የሚሆነው ከመንፈስ ቅዱስ የተነሣ እንደሆነ መስክሯል።

ለ. የኤልሳቤጥ ሰላምታ

የዘካርያስ ሚስት እርስዋም የመጥምቁ ዮሐንስ እናት ቅድስት ኤልሳቤጥ ወዳጇና ዘመዷ የሆነች ድንግል ማርያም ልትጠይቃት ወደ ቤቷ በሄደች ጊዜ የማርያምን የሰላምታ ቃል

Copyright © 2009 Debre Selam Medhanealem Ethiopian Orthodox Tewahedo Church 4401 Minnehaha Avenue South Minneapolis, Minnesota 55406 Tel. (612) 721-1222 (U.S.A)

ስትሰማ በማኅጸኗ ውሰጥ ያለው ጽንስ ዘለለ ፤ እርሷም (ኤልሳቤጥም) "የጌታዬ እናት ወደ እኔ ትመጣ ዘንድ እንዴት ይሆንልኛል? እነሆ የሰላምታሽ ድምጽ በጆሮዬ በመጣ ጊዜ ጽንሱ በማኅጸኔ በደስታ ዘሎአልና ከጌታ የተነገረላት ቃል ይፈጸማልና ያመነች ብጽእት ናት" አለች። ሉቃ. ፩ ፥፴፱-፵፭

እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም የጌታ እናት መሆኗን መንፈስ ቅዱስ ለኤልሳቤጥ ገለጸላትና የጌታዬ እናት አለች ፤ በማኅጸኗም ያለው ጽንስ ከእርሱ በኋላ ለሚወለደው ለጌታውና ለእናቱ በደስታ ዘለለ/ሰገደ ራሷ ድንግል ማርያምም የመልአኩን ብስራት ከተቀበለች በኋላ "ትውልድ ሁሉ ብጽዕት ይሉኛል" ሉቃ.፩ ፥፵፱ በማለት ተናግራለች።

ስለዚህ ቅድስት ድንግል ማርያም በእግዚአብሔር የተመሰከረላት የሰው ልጆች የድኅነት መሠረት ናት ፤ እኛም <u>ጸጋን የተመላሽ ድንግል ሆይ ለምኝልን</u> እያልን ዘወትር እንጠራታለን።

ሐ. <u>የመስቀል ስጦታ</u>

ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለሰው ልጆች ሲል በመስቀል ላይ ተሰቅሎ ሳለ በወዳጁ በቅዱስ ዮሐንስ አማካኝነት ለሰው ሁሉ የሰጠው ታላቅ ስጦታ እመቤታችንን ነው። ዮሐ.፲፱ ፥፳፮-፳፯

ሰዎች ዛሬ በጌታችን የልደት ዘመን የተለያዩ ስጦታዎችን ይሰጣጣሉ ፤ ለነፍስ የማይጠቅም አላቂ ሃላፊ ቁሳቁስ ይሰጣጣሉ ፤ የሚኮነን ልምድ ባይሆንም ከጌታ የተሰጠችንን ታላቅ ስጦታ ግን ከሁሉ አስቀድሞ መቀበል ይገባል ፤ እመቤታችን በልደቱ ልደት ጊዜ አብራው ነበረች ፤ በስደቱ ጊዜም አብራው የተንገላታች ነች ፤ በመጨረሻው ሰዓት በአስጨናቂው ጊዜ በመስቀሉም አጠገብ የተገኘች እርሷ ናት ፤ ስለዚህ ለኛም ዘወትር የማትለየን እናታችን መሆኗን መረዳት ይገባናል።

<u>**ጥያቄ፦**</u>

<u>ከላይ የተማርነውንና ያነበብነውን መሠረት በማድረግ ትክክለኛውን መልስ ስጥ/ጪ</u>

፩. ቅድስት ድንግል ማርያም ለምን የመጀመሪያቱ ምድር ተባለች ?

- ሀ. ከፍጥረታት ሁሉ በፊት ስለተፈጠረች
- ለ. በአምላክ ሕሊና ታስባ ትኖር ስለነበር
- ሐ. ምድር መጀመሪያ ያለምንም ዘር እንዳፈራች እርሷም ያለዘር ልጇን ኢየሱስ ክርስቶስን ስለወለደች
- መ. ሁሉም

፪. ቅድስት ድንግል ማርያም በሲና ሐመልማል ለምን ተመሰለች ?

- ሀ. በግብጽ በረሃ በመሰደዷ
- ለ. በሲና በረሃ የሚበቅል ዕጽ ለምለም ስለሆነ
- ሐ. የምታምር እጽ ስለሆነች
- መ. እሳት የሆነውን መለኮት እግዚአብሔር ወልድን በማኅጸኗ ስለተሸከመች

፫. እመቤታችን ለምን በኤልሳዕ ማሰሮ ተመሰለች ? አብራራ/አብራሪ

Copyright © 2009 Debre Selam Medhanealem Ethiopian Orthodox Tewahedo Church 4401 Minnehaha Avenue South Minneapolis, Minnesota 55406 Tel. (612) 721-1222 (U.S.A) 

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በማዛመድ መልስ/መልሽ

------፩. የጌታዬ እናት ወደ እኔ ትመጣ ዘንድ እንዴት ይሆንልኛል?
------፪. አጸ-ሳቤቅ
------፫. ብስራተ ቅዱስ ገብርኤል
------፬. እመቤታችንን በታጠረች ተክል የመሰለት ታሪክ
------፭. ዘፍ. ፩ ፥፲፩
------፮. ፪ነገ.፪ ፥፲፱-፳፩
------፯. ዘጸ.፫ ፥፩-፭
------፰.በማኅጸን ሳለ ለጌታችንና ለእናቱ የሰገደ

ሀ. ሐረግ
ለ. የሲና ሐመልማል
ሐ. ቅዱስ ዮሐንስ
መ. ዘር ያልተዘራባት እርሻ
ሠ. የኤልሳ ማሰሮ
ረ. ቅድስት ኤልሳቤጥ
ሰ. ጠቢቡ ሰሎሞን
ሸ. ሉቃ.፩ ፥፳፮-፳፰

## ፭. የቅድስት ድንግል ማርያም ቅድስና ድንግልናና አማላጅነት

### ሀ. ቅድሰናዋ

እግዚአብሔር ቅዱስ አምላክ ነው ፤ ማደሪያውም ሁሉ ቅዱስ ነው እግዚአብሔር በበረከትና በረድኤት ያደረባቸው ሰዎች ቦታዋችና ነዋያት ሁሉ ቅዱስ የሚል ቅጽል ይሰጣቸዋል። እመቤታችን ድንግል ማርያም ደግሞ እግዚአብሔር በበረከትና በረድኤት ብቻ ሳይሆን በሥጋም ያደረባት ናትና ቅድስት/ቅድስተ ቅዱሳን ትባለለች ፤ ቅድስናዋምበሥጋ ፣ በነፍስና በሕሊናዋም ጭምር ነው። ነብዩ ዳዊትም "ልዑል ማሪያውን ቀደሰ" መዝ. ፵፭ ፥፬-፭ በማለት አስቀድሞ በፈጣሪ ዘንድ የተቀደሰች መሆኗን ይናገራል። መልአኩ ቅዱስ ገብርኤልም "ከሴቶች ተለይተሽ የተባረክሽ ነሽ የማኅጸንሽም ፍሬ የተባረከ ነው" ሉቃ. ፩ ፥፳፰ በማለት ቅድስናዋን መስክሯል።

### ለ. ድንግልናዋ

ነብዩ ሕዝቅኤል በምዕራፍ ፵፬ ፥፪ ላይ "እግዚአብሔር ይህ በር ተዘግቶ ይኖራል እንጂ አይከፈትም ሰውም አይገባበትም የእስራኤል አምላክ እግዚአብሔር ገብቶበታልና ተዘግቶ ይኖራል" ይላል። ይህ ቃል የተነገረው ለእመቤታችን ለቅድስት ድንግል ማርያም ነው ሰው የሆነው አምላክ ኢየሱስ ክርስቶስ በገባበት በዚያ በር ማንም አልገባም ማንም አልወጣም።

የበኵር ልጇን እስክትወልድ አላወቃትም ተብሎ ቢነገርም ማቴ. ፩ ፥፳፭ በኵር ሁል ጊዜ ተከታይ አለው ማለት እንዳልሆነ ይህ የነብዩ የሕዝቅኤል ትንቢት ያረጋግጣል ፤ ነብዩ ኢሳይያስ በትንቢቱ ኢሳ.፯ ፥፲፬ ላይ "እነሆ ድንግል ትጸንሳለች ወንድ ልጅም ትወልዳለች" ይላል ፤ ቅዱስ ሉቃስ በወንጌል እንደጻፈው የመልአክት አለቃ ቅዱስ ገብርኤል የጌታን ከእርሷ መወለድ ሊያበስራት በተላከ ጊዜ "ወደ አንዲት ድንግል ተላከ የድንግሊቱም ስም ማርያም ነበረ ይላል"፤ ሉቃ.፩ ፥፳፯ በተጨማሪም በመኃልይ ፬ ፥፲፪-፲፭ ፤ ሉቃ.፩ ፥፴፬ ላይ ስለድንግልናዋ ተጽፎ ይገኛል።

ለዚህም ነው እመቤታችንን ከሴቶች ሁሉ ተለይተሽ የተባረክሽ ነሽ እያልን ዘወትር የምናመሰግናት ፤ የተመሰከረላት ፍጹም ድንግል ናትና ፤ ልጇን ኢየሱስ ክርስቶስን ከመጽነሷ በፊት ፣ በጸነሰች ጊዜ ፣ ከጸነሰችም በኋላ ፣ ከመውለዷ በፊት ፣ በወለደች ጊዜ ፣ ከወለደችም በኋላ ፣ ፍጹም ድንግል ናት። ሌሎች ሴቶች ከወለዱ በኋላ እናት እንጂ ድንግል አይባሉም ፤ እርሷ ግን እናትም ድንግልም ናት።

Copyright © 2009 Debre Selam Medhanealem Ethiopian Orthodox Tewahedo Church 4401 Minnehaha Avenue South Minneapolis, Minnesota 55406 Tel. (612) 721-1222 (U.S.A)

ሐ. <u>አማላጅነቷ</u>

ማማለድ ማለት በሁለት ወገኖች መካከል ሆኖ ለአንደኛው ወገን (ለበዳዩ) ከተበዳዩ ዘንድ ይቅርታ መለመን ወይንም ማስታረቅ ማለት ነው። ዘወትር በደለኛና ኃጢያተኛ የሆነ ሰው ወደ ፈጣሪው የሚያቀርበው ይቅርታ በቶሎ እንዲሰማለት ወገኖቹ ለሆኑት ቅዱሳን የሚያቀርበው የአስታርቁኝ ጩኸት ምልጃ ይባላል። ቅዱሳንም ለእግዚአብሔር ቅርብ ስለሆኑና የእግዚአብሔር ዓይኖቹም ዘወትር ወደ እነርሱ ስለሆኑ ቶሎ ይሰማቸዋል ፤ የለመኑትንም ይፈጽምላቸዋል። መዝ. ፴፫ ፥፲፭

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስም በ፪ኛ ቆሮ. ፭ ፥፲፰ ላይ "ነገር ግን የሆነው ሁሉ በክርስቶስ ከራሱ ጋር ካስታረቀን የማስታረቅም አገልግሎት ከሰጠን ከእግዚአብሔር ነው" ይላል። በቅዱስ መጽሐፍ ውስጥ የእመቤታችን የቅድስት ድንግል ማርያም አማላጅነት ደግሞ በገሃድ የታየበት የቃና ዘገሊላ የሰርግ ቤት ነው ውኃው ወደ አማረ የወይን ጠጅ የተቀየረው በእርሷ አማላጅነት ነው። ዮሐ.፪ ፥፩-፲

<u>**ጥያቄ፦**</u>

<u>ከላይ የተማርነውንና ያነበብነውን መሠረት በማድረግ ትክክለኛውን መልስ ስጥ/ጪ.</u>

፩. ድንግል ማርያም ቅድስት የምትባለው
- ሀ. አባትና እናቷ ፣ አያትና ቅድም አያቶቿ ቅዱሳን ስለሆኑ ነው
- ለ. በንጽሕና ስለኖረች ነው
- ሐ. አምላክ ማደሪያው ስላደረጋት ነው
- መ. ሁሉም መልስ ይሆናል

፪. አምላክ በቅድስት ድንግል ማርያም ላይ ያደረው
- ሀ. በረድኤት ብቻ ነው
- ለ. በበረከት ብቻ ነው
- ሐ. ከሥጋዋ ሥጋን ከነፍሷ ነፍስን ነስቶ ነው

፫. ቅድስት ድንግል ማርያም
- ሀ. በኅሊናዋ በሥጋዋና በነፍሷ ድንግል ናት
- ለ. በሥጋዋና በነፍስዋ ብቻ ድንግል ናት
- ሐ. በሥጋዋና በሕሊናዋ ብቻ ድንግል ናት
- መ. መልስ የለም

፬. ስለ ቅድስት ድንግል ማርያም ድንግልና የተናገረው
- ሀ. ቅዱስ ገብርኤል
- ለ. ነብዩ ሕዝቅኤል
- ሐ. ነብዩ ኢሳይያስ
- መ. ሁሉም

፭. ለሚከተሉት ጥያቄዎች ማብራሪያ ስጥ/ጪ.

የቅድስት ድንግል ማርያም ድንግልና ከሌሎች ሰዎች ድንግልና የሚለየው እንዴት ነው?

Copyright © 2009 Debre Selam Medhanealem Ethiopian Orthodox Tewahedo Church 4401 Minnehaha Avenue South Minneapolis, Minnesota 55406 Tel. (612) 721-1222 (U.S.A) 

## ፯. በዓላተ እግዝእትነ ማርያም

እመቤታችን በዓመት ፴፫ በዓላት አሏት እነርሱም በተአምረ ማርያም ላይ ተጠቅሰዋል፡-

፩. ነሐሴ ፯ ቀን የተጸነሰችበት
፪. ነሐሴ ፲፮ የፍልሰቷ መታሰቢያ እስከ ፳፩ በዓሏ ነው
፫. መስከረም ፲ የእመቤታችን ሥዕል የመሪና ቦታ ወደምትሆን ጴጼንያ ወደምትባል አገር ገብታ የተቀመጠችበት ነው
፬. መስከረም ፳፩ ቀንም ትከብራለች
፭. ጥቅምት ፳፩ ቀንም ትከብራለች
፮. ኅዳር ፮ ቁስቋም በምትባል አገር ገብታ የተቀመጠችበት ነው
፯. ኅዳር ፳፩ ዘካርያስ የመቅረዝ ፋና ሲያበራ ያየበት
፰. ታኅሳስ ፫ ቤተመቅደስ የገባችበት
፱. ታኅሳስ ፳፩ ቀንም ትከብራለች
፲. ታኅሳስ ፳፪ ደቅስዮስ የሚባል ኤጲስቆጶስ በዓሏን ያከበረበት
፲፩. ታኅሳስ ፳፰/፳፱ መድኃኒታችንን ኢየሱስ ክርስቶስን የወለደችበት
፲፪. ጥር ፳፩ የእረፍቷ ቀን ነው
፲፫. የካቲት ፲፮ የምሕረት ቃል ኪዳን ከልጇ የተቀበለችበት
፲፬. የካቲት ፳፩ ትከብራለች
፲፭. መጋቢት ፳፩ ትከብራለች
፲፮. መጋቢት ፳፱ ልጇን የጸነሰችበት
፲፯. ሚያዝያ ፳፩ በዓሏ ነው
፲፰. ግንቦት ፩. ልደቷ ነው
፲፱. ግንቦት ፳፩ ደብረ ምጥማቅ በምትባል ቤተክርስቲያን ከመላእክት ፣ ከጻድቃንና ከሰማዕታት ጋር ተገልጻ ለአምስት ቀናት ከ፳፩-፳፭ ድረስ የታየችበት ነው።
፳. ግንቦት ፳፬ ወደ ግብጽ አገር የገባችበት ነው
፳፩. ግንቦት ፳፭ ልጇ የደረቁ በትሮችን ተክሎ ያለመለመበት ነው
፳፪. ሰኔ ፰ ልጇ ለሕሙማን ድኅነት የሚሆን ውኃን ከአለት ላይ ያፈለቀበት ነው
፳፫. ሰኔ ፳ ሐዋርያት የተሰበሰቡበት ልጇም ቤቷን ለመሥራት የወረደበት
፳፬. ሰኔ ፳፩ ቤቷን ያከበረበት
፳፭. ሐምሌ ፳፩ ቀንም ትከብራለች

### ጥያቄ፡-

ከላይ የተማርነውንና ያነበብነውን መሠረት በማድረግ ትክክለኛውን መልስ ስጥ/ጪ

፩. እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም የተጸነሰችው ፣የተወለደችው ፣ ያረፈችው (የሞተችው) ፣ያረገችው መቼ ነው ? አሁንስ ያለችው የት ነው ?
፪. ስለነሐሴ ፲፮ ቀን የድንግል ማርያም በዓል ታሪክ ባጭሩ አብራራ/ሪ።

ይቀጥላል....

ለዝግጅት የዋሉ ምንጮች፡-

-መጽሐፍ ቅዱስ
-ወለዲተ አምላክ በመጽሐፍ ቅዱስ (ዲያቆን ደጀኔ ሺፈራውና ዲያቆን እሸቱ ታደሰ)
-ነገረ ማርያም (ሊቀጠበብት ሐረገወይን አገዘ እና ቀሲስ እሸቱ ታደሰ)
-ክብረ ቅዱሳን (ከአባ ገብርኤል)
-ተዓምረ ማርያም

Copyright © 2009 Debre Selam Medhanealem Ethiopian Orthodox Tewahedo Church 4401 Minnehaha Avenue South Minneapolis, Minnesota 55406 Tel. (612) 721-1222 (U.S.A)